የመንግሰት ግዥና ንብረት ባለስልጣን

የካይዘን ፍልስፍናን

አጠቃቀም ሰነድ

ህዳር/ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

1. መግቢያ---------- 2
2. የባለስልጣኑ ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች---------- 4
3. የሰነዱ ዓላማ---------- 5
4. ዝርዝር ዓላማዎች---------- 5
5. የሰነዱ አስፈላጊነት---------- 6
6. የተፈጻሚነት ወሰን ---------- 6
7. ትርጉም---------- 7
8. ካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍና ምንነት---------- 7
9. የካይዘን ፍልስፍና የመጠቀም ጠቀሜታ---------- 8
10. የካይዘን የስራ አመራር ፍልስፍና 5ቱ "ማ"ዎች---------- 10
    - 10.1. ማጣራት- Sort---------- 10
    - 10.2. ማደራጀት- Set-in-order---------- 10
    - 10.3. ማፅዳት-Shine---------- 11
    - 10.4. ማላመድ-Standardize---------- 12
    - 10.5. ማዝለቅ-Sustain---------- 12
11. የካይዘን ዕቅድ ደረጃ ፍሰት ማደራጀት---------- 12
12. የበጀት ዝግጅት---------- 20
13. የካይዘን ሥራ አመራር ትግበራ ክትትልና ድጋፍ---------- 20

1. መግቢያ

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነትን መወጣት እንዲያስችለው የአሰራር ሥርዓትን በማሻሻል ወደ ተግባር በመለወጥ ባለፉት ዓመታት የመንግስት ግዥ አፈፃፀምና ንብረት አስተዳደርን ለማሻሻል የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት እና ፕሮጀክቶች በማቀድ በሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ አዎንታዊ ስራዎችን ያከናወነ ቢሆንም፤ በየወቅቱ እያደገ በሚሄደው የዜጎች ሁለንታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ወይም ጉዳዮች ግምት ውስጥ በማስገባት በግዥ አፈፃፀምና ንብረት አስተዳደር ሂደት የለውጥ ሂዳት ከሆነው የካይዘን ፍልስፍናን በመተግበር የንብረት አጠቃቀምንና አስተዳደርን ማዘመን የሚያስችል ሰነድ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር መለወጥ በዝግጅት ምዕራፍ ታቀዶ ከሚከናወኑ አበይት ተግባራት መካከል አንዱ ነው።

በተቋማችን ውስጥ ምቹ የሥራ አካባቢ መፍጠር ሠራተኞች ለሥራ ያላቸውን ተነሳሽነት በመጨመር የተሰጣቸውን ተግባራት እና ተልዕኮ በብቃት እና በጥራት እንዲፈጽሙ ያግዛል። ከዚህ በተጨማሪም የእርስ በርስ ትብብርንና መግባባትን በማጎልበት የተቋሙን ተልዕኮ በውጤታማነት ለመፈጸም ያስችላል። በሌላ በኩልም ምቹ የሥራ አካባቢ ወደ ተቋሙ የሚመጡ አገልግሎት ፈላጊዎች ያለ እንግልትና ውጣ ውረድ የሚፈልጉትን አገልግሎት በጥራትና በቅልጥፍና ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል።

በመሆኑም ባለስልጣኑ የተሰጡትን ኃላፊነትና ተግባርን በመወጣት ረገድ የሚያከናውናቸውን ዋና ዋና ተግባራት የመንግስት ግዥና ንብረት ሥራዎችን ዲጂታላይዝ ማድረግ፣ የግዥና ንብረት አቅም ግንባታ አጣናክሮ ማስቀጠል፣ የአዲትና ክትትል ስራ እንዲሁም አቤቱታዎችና የጥፋተኝነት ሪፖርቶች ወቅታዊ ምላሽ መስጠትን፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጣጣመ የግዥና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር የሚያስችሉ ሥራዎችን ማከናወን የሚያስችል ዋና የለውጥ ተዋናይ የሆነውን የሰው ኃይሉን በተለይም ፈጻሚውን ማጎልበት እንደሚገባ ለመረዳት ተችሏል።

በዚሁ መሰረት ባለፉት ዓመታት የተቋሙን የሰው ኃይል ልማት ካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍናን ትኩረት ባደረገ መልኩ ለተቋሙ የተሰጡትን ኃላፊነቶችና ተግባራትን ለመወጣት በሚያስችል ቁመና ለማደረጃትና ለማብቃት የተደረገው ጥረት በቂ ባይሆንም በአዲሱ አዋጅ የተሰጠውን የስልጠን ወሰን በአግባቡ ለመወጣትና ሀገራዊ ሪፎርሞችን ለማስፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ የሰው ሀብት ልማት ውስጥ ካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍናን በየደረጃው ለለውጥ

ማብቃት የሚያስችል ሰነድ በማዘጋጀት ወደ ተግባር መለወጥ ጠቀሜታው የጎላ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል።

በዚሁ መሰረት የካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍና በባለስልጣኑ ሥራ ላይ መዋል የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ተወዳዳሪና ዉጤታማ ከማድረግ ባሻገር የጋራ ተልዕኮን ከማሳካት አኳያ ከፍተኛና መካከለኛ አመራርን እንዲሁም ሠራተኞችን በማስተሳሰር ሰው በማንኛዉም ቦታ እና ጊዜ ለውጥና መሻሻልን አስቦ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርግ፣ ፈጠራና አዳዲስ አስተሳሰብን የሚያበረታታና ሰፊ የለውጥ፣ የጥራትና የምርታማነት ንቅናቄን በመፍጠር ስኬታማ የሚያደርግ የአመራር ፍልስፍና ነው።

ለዚህም ምክንያቱ ሰዎች የአንድ ተቋም ከፍተኛው ሀብት ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው፣ሰዎች ለተቋማቸው ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉት በተለመደው ተቋማዊ መዋቅር የሰው ኃይል አሰላለፍ የተዋረድ አሠራር ላይ በተመሠረተ የሥራ ትዕዛዝ በመስጠትና በመቀበል አመራር ብቻ ሳይሆን በሥራ ቦታ ላይ እንደ አንድ የሥራ ክፍል ቡድን እና ግለሰብ ስለሚሰጡት አገልግሎት እና ስለአሠራራቸው የተሻለ ሀሣብ እንዲያመነጩ፣ እንዲመክሩ፣ እንዲተገብሩ፣ ለውጣቸውን እንዲያዩ፣ ከለውጡም እንዲቋደሱ የሚያስችል የሥራ አካባቢ ሊፈጠርላቸው ነው።

በመሆኑም መግቢያ፣ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴት፣ ዓላማ፣ ዝርዝር ዓላማ፣ የሰነዱ አስፈላጊነት፣ የተፈጻሚነት ወሰን፣ ትርጉም፣ ካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍና ምንነት፣ የካይዘን ፍልስፍና የመጠቀም ጠቀሜታ፣ የካይዘን የስራ አመራር 5ቱ "ማ"ዎች መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ነው።

2. የባለስልጣኑ ራዕይ፣ ተልዕኮና ዕሴቶች

2.1 ራዕይ (Vission)

በ2022 ዓ.ም በአፍሪካ ተፎካካሪ የመንግስት የግዥና ንብረት ተቆጣጣሪ ተቋም ሆኖ መገኘት

2.2 ተልዕኮ (Mission)

የመንግስት ግዥና ንብረት ሥርዓትና ቁጥጥርን በማጠናከር ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጥቅም እንዲያስገኝ ማስቻል!!

2.3. ዕሴቶች ((values)

- ትኩረት ለዘመናዊ የኤሌክትሮኒክ ግዥና ንብረት ስርዓት
- የላቀ የአገልግሎት ጥራት፣
- ፍትሃዊነት፣ ቅንነት፣ ታማኝነት እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን መስራት፣
- አርዓያነት፣
- የቡድን ሥራ ለውጤታማነት፣
- ትኩረት ለባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች፣

3. የሰነዱ ዓላማ

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት መሰረት በማድረግ የተቋሙን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት በየዓመቱ የሚታቀዱ ስትራቴጂያዊ ግቦችን በውጤታማነትና በቀልጣፋነት ለመወጣት የሚያስችል የሰው ሀብት ልማት ውስጥ የስራ አከባቢን የተደራጀ እና ወጥ የሆነ በማድረግ ለለውጥ ያለው ሚና ማሳደግ የሚያስችል ሰነድ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ ማዋል ነው።

4. ዝርዝር ዓላማዎች

1. በባለስልጣኑ የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ሥራ ላይ በማዋል የሥራ አካባቢ ምቹነት እና ዘመናዊ የቢሮ አደረጃጀት ሥርዓትን መገንባት
2. በባለስልጣኑ የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ሥራ ላይ በማዋል የሠራተኞችን የችግሮች በማቃለልና በመፍታት አቅማቸውን ለማሳደግ፣
3. በባለስልጣኑ የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ሥራ ላይ በማዋል የጋራ ብልጽግና ወይንም ዕድገት መርህን ለመከተል፣
4. በባለስልጣኑ የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ሥራ ላይ በማዋል በሰራተኞች ቀና አስተሳሰብን ለመፍጠርና ለማስረጽ፣
5. በባለስልጣኑ የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ሥራ ላይ በማዋል የሥራ ላይ ሥነ ምግባርን ለመገንባት፣
6. የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ሥራ ላይ በማዋል የተገልጋዮችን ፍላጐት ማዕከል ያደረገ አሠራርን በመከተል፣ የሥራ ፍላጐትን ለማነሳሳት፣
7. የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ሥራ ላይ በማዋል ለሥራ ከፍተኛ ሁኔታ የሠራተኞችን የሥራ ተነሳሽነትን ለመፍጠር፣
8. በባለስልጣኑ የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ሥራ ላይ በማዋል የግል ኃላፊነትን በአግባቡ የመገንዘብና የመወጣት ስሜትን ለመፍጠር፣
9. በባለስልጣኑ የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ሥራ ላይ በማዋል እያንዳንዱ ሠራተኛ ከሥራ ክፍልና ከተቋም ባሻገር የህብረተሰብ ዕድገትን ማምጣት አስተዋጽኦ እንዳለው ለማስገንዘብ፣

5. የሰነዱ አስፈላጊነት

በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን ፅንሰ ሃሳብ ሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል የስራ አከባቢን የተደራጀና ወጥ የሆነ ለማድረግ የሚጠቅም መሳሪያ መሆኑ፣ ቀጣይነት ያለዉ የማያቋርጥ ለዉጥ ለማምጣት የሚያገለግል መሳሪያ መሆኑ፣ ብክነትን ለማስወገድ የሚረዳ በመሆኑ፤ የሠራተኛውንና የሥራ አመራሩን የሚያቀራርብ መሳሪያ መሆኑ፣ በሠራተኞች መካከል የሥራ ትብብርን የሚፈጥር መሳሪያ በመሆኑ፣ በራስ መተማመንን የሚፈጥር፣ መሪዎችን ለማፍራት የሚረዳ፣ ተተኪዎችን ለማፍራትና የሥራ ፈጠራን የሚያበረታታ መሳሪያ መሆኑ እና የሥራ ዕርካታን የሚያስገኝ መሳሪያ መሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በመሆኑም በባለስልጣኑ ውስጥ ያለውን ንብረት የሚፈለገውን ከማይፈለገው በመለየት የማይፈለገውን በአግባቡ በማስወገድ የሥራ አካባቢን ደረጃ እና ደንብ በመጠበቅ ዘላቂ በማድረግ የስራ አመራር ፅንሰ ሃሳብ የሆነውን ካይዘን በመተግበር የስራ አከባቢን የተደራጀ እና ወጥ የሆነ ለማድረግና ቀጣይነት ያለዉ የማያቋርጥ ለዉጥ በማምጣት ብክነትን ለማስወገድ የሚረዳ መሳሪያ መሆኑ ደግሞ ካይዘንን በመተግር ሥራ ላይ ማዋል በጣም አስፈላጊ መሳሪያ ያደርገዋል።

6. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ የካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍና ሰነድ ተፈፃሚ የሚሆነው በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ውስጥ ያሉ በሁሉም ሠራተኞችና የሥራ ክፍሎች ላይ የሚተገበር ነው።

7.ትርጉም

ካይዘን የሚለው ቃል የጃፓን ቃል ሆኖ ካይ ማለት ለውጥ ሲሆን ዘን ማለት ደግሞ የተሻለ ማለት ሲሆን ቀጣይነት ያለው የተሻለ ለውጥ ማለት እንደሆነ ትርጓሜው ሲያመለክት፤ የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍና ትኩረት የሚሰጠው ነባራዊ ሁኔታን በመረዳትና የስራ አካባቢን ለማሻሻል የሚረዳ መሳሪያ ነው።

8.ካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍና ምንነት

የካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍና ለውጥ እንዲያመጡ ከሚያስችሏቸው ዘዴዎች መካከል የሚከተሉት በመሠረታዊነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

- ዋና የለውጥ ተዋናይ አድርጎ የሚወስደውም የሰው ኃይሉን በተለይም ፈጻሚውን ነው፣
- የካይዘን የለውጥ መርሆ አንድም ቀን ቢሆን ያለ ለውጥ ማለፍ የለበትም የሚል ነው፣
- የካይዘን የለውጥ ቡድን የማያቋርጥ የጥራት መሻሻልን ማዕከል ያደረገና ከታች ጀምሮ ያለውን ሰራተኛ የሚያቅፍ ቡድን ነው፣
- የካይዘን የለውጥ ቡድን ፍልስፍና የሚመነጨው ከአሳታፊነት እና ሰብዓዊ ተኮር ከሆነ አመራር /Participative and Human Oriented Management/ ሲሆን የዚህ አመራር ፍልስፍና ለሰዎችና ለፍላጐታቸው ትኩረት የሚሰጥ ነው፣
- ለዚህም ምክንያቱ ሰዎች የአንድ ተቋም ከፍተኛው ሀብት ናቸው ተብሎ ስለሚታመን ነው፣
- ሰዎች ለተቋማቸው ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉት በተለመደው ተቋማዊ መዋቅር የሰው ኃይል አሰላለፍ የተዋረድ አሠራር ላይ በተመሠረተ የሥራ ትዕዛዝ በመስጠትና በመቀበል አመራር ብቻ ሳይሆን በሥራ ቦታ ላይ እንደ አንድ የሥራ ክፍል ቡድን እና ግለሰብ ስለሚሰጡት አገልግሎት እና ስለአሠራራቸው የተሻለ ሀሣብ እንዲያመነጩ ፣ እንዲመክሩ ፣ እንዲተገብሩ ፣ ለውጣቸውን እንዲያዩ ፣ ከለውጡም እንዲቋደሱ የሚያስችል የሥራ አካባቢ ሲፈጠርላቸው ነው፡፡
- የሠራተኞችን የችግሮች/ማነቆዎች የማቃለልና የመፍታት አቅማቸውን በማሳደግ የጋራ ብልጽግና ወይንም ዕድገት መርህን የሚከተል ነው፤
- በሠራተኞች መካከል ቀና አስተሳሰብን በመፍጠርና በማስረጽ የሥራ ላይ ሥነ-ምግባርን መገንባት ነው፡፡
- የተቋሙን ተገልጋዮች ፍላጐት ማዕከል ያደረገ አሠራርን በመከተል የሥራ ፍላጐትን ማነሳሳት ነው፡፡
- የግል ኃላፊነትን በአግባቡ የመገንዘብና የመወጣት ስሜትን በመፍጠር ለሥራ ከፍተኛ መበረታታትን ለመፍጠር ነው፡፡

- እያንዳንዱ ሠራተኛ ከሥራ ክፍልና ከተቋም ባሻገር የህብረተሰብ ዕድገትን ማምጣት አስተዋጽኦ እንዳለው ማስገንዘብ ናቸው።

9. የካይዘን ፍልስፍና የመጠቀም ጠቀሜታ

የባለስልጣኑ ሠራተኞች አዎንታዊ የሆነ የዕድገት አስተሳሰብ እንዲኖራቸው፣ እንዲሁም አቅማቸውን በማዳበር ላይ ማተኮር እና የተቋሙን ተልዕኮ ማሳካት እንዲችሉ ምቹ የሥራ አካባቢ እና የሥራ ላይ ደህንነት የተረጋገጠ ቦታ በካይዘን እንደሚተገበር እውን ነው። ይህ ደህንነት የሚረጋገጠው ምቹ እና ሳቢ የሥራ ከባቢ በመፍጠር መሆኑ ይታመናል። የካይዘን ስራ አመራር ፍልስፍናን በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ተግባራዊ በደረግ በባለስልጣኑ ውስጥ ባሉትሠራተኞችና የሥራ ክፍሎች የሚከተሉትን ጠቀሜታ ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፤

- ሠራተኛውንና የሥራ አመራሩን ለማቀራረብ ይጠቅማል፤
- በሠራተኞች መካከል የሥራ ትብብርን በመፍጠር የሥራ ዕርካታን ያስገኛል፣
- የሠራተኞችን በራስ መተማመንን በመጨመር የሥራ ተነሳሽነትን ይፈጥራል፣
- ተተኪ መሪዎችን ለማፍራትና የሠራተኞች የሥራ ፈጠራን ለማበረታታት ይጠቅማል፤
- ቀጣይነት ያለዉና የማያቋርጥ ለዉጥ ለማምጣት መሰረት ነዉ::
- ካይዘን ሥራ አመራር ብክነትን ለማስወገድ የሚረዳ መሳሪያ ነዉ::
- ካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍናን በመጠቀም ፋይሎችንና ቁሶችን ለመፈለግ የሚባክን ጊዜ ለመቀነስ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል፤
- ሰራተኞች ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳትን በመቀነስ ከመጠን በላይ የሆነ ክምችትን ለመቀነስ ይጠቅማል፤
- የመስሪያ ቦታው የፀዳ፣ ጉዳት የማያደርስ እና ምቹ እንዲሆን ያደርገዋል፤
- በስራ ላይ የሚከሰቱ ጫናዎችን እና አለመስማማቶችን ያስወግዳል፤
- በተቋሙ ከስራ ክፍል ሰራተኞች ጋር በቀላሉ በማግባባት የስራ እርካታ እንዲኖር ያደርጋል፤
- የስራ ቦታ ምን መምሰል እንዳለበት ጥሩ ግብዓት እንዲፈጠር እድል ይሰጣል፤

- ሁሉን ነገር ረስተን ትኩረታችን ስራው ላይ ብቻ እንዲሆን ያስችለናል።
- የሰራተኞችንየስራ ሞራል በማነሳሳት እና የጋራ ስራን በማበረታታት የባለቤትነት ስሜትን ይፈጥራል፤
- ወጥ የሆነ የስራ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ ብክነት መቀነስ እና ግድፈት ባዶ በማድረግ ጥራት ያሳድጋል
- ብክነትን ባዶ በማድረግ ወጪን ይቀንሳል
- ማዘግየት እንዳይኖር በማድረግ ጥራት ያለው አገልግሎት አሰጣጥ ወቅቱን ጠብቆ ለተገልጋዮች እንዲደርስ ያስችላል፤
- ምንም ዓይነት ጉዳት እናደይኖር በማደረግ የሥራ ቦታ ደህንነትን ይጨምራል
- የተገልጋይ ቅሬታ እንዳይኖር በማድረግ ከፍተኛ የሆነ እምነት እና በራስ መተማመን ያመጣል እና ከመጠን በላይ የሆነ የግምጃ ቤት ክምችትን ለማስወገድ ይረዳናል፤

10. የካይዘን የስራ አመራር ፍልስፍና 5ቱ "ማ"ዎች

የካይዘን የስራ አመራር ፍልስፍና ፅንሰ ሃሳብ ከአምስት የአማርኛ ቃላቶች የመጀመሪያ "ማ" ፊደሎች በመውሰድ የተሰየመ ነው። የከይዘን ማስጀመሪያ መሳሪያ ሆኖ የስራ አከባቢን የተደራጀ እና ወጥ የሆነ ለማድረግ የሚጠቅም ቀጣይነት ያለዉ የማያቋርጥ ለዉጥ ለማምጣት የሚያስችል መሳሪያ ነዉ:: አምስቱ በ"ማ" ፊደሎች የተሰየሙት የካይዘን ሥራ አመራር ፅንሰ ሃሳብ በመሆን የተሰየሙት ማጣራ (sort)፣ ማደራጀት (set in order)፣ ማፅዳት (shine)፣ ማላመድ (standardize) እና ማዘለቅ (sustain) ናቸው።

10.1. ማጣራት- Sort

ማጣራት ማለት የስራ ቦታዎቻችን፣ በማከማቻ ቦታና በቢሮ የሚገኙ ሁሉም ግብአቶች እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶች በሥራ ቦታችን ላይ የማይፈለጉ ነገሮችን ለይቶ በማስወገድ በቦታው ለምንሰራው ሥራ የሚያስፈልገንን ቁስ ብቻ በምንፈልገዉ መጠን ማስቀረት ማለት ነው። በካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍና ከሆነው ማጣራትን ከመተግበር የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣል፦

- ቦታ፣ ጊዜ፣ ገንዘብ፣ ሃይል እና ሌሎች ሃብቶችን በአግባቡ ለማስተዳደር እና ለመጠቀም ስለሚያስችል በግምጃ ቤቶቻችን፣ በቢሮ እና አገልግሎት መስጫ ቦታዎች የሚያጋጥሙ ችግሮች

እንዲቀንሱ እንዲሁም እንዲወገዱ ያስችላል።

- በተቋሙ ሰራተኞች መካከል ያለዉ የመግባባት ሂደትን ይጨምራል፤
- የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት እና መልካም አስተዳደር እንዲሻሻል ያደርጋል

10.2. ማደራጀት (Set-in-order)

ማደራጀት ማለት የሚያስፈልጉ ቁሶች ለመፈለግ፣ ለመጠቀም፣ በቦታቸዉ ለመመለስ የሚያስችል ምልክት በመጠቀም ለእያንዳንዷ ነገር ቦታ ማዘጋጀት በአግባቡ ማስቀመጥ ማለት ነው። ማደራጀት በማጣራት ሂደት ውስጥ ለተለዩት ዶክመንቶች፣ የሥራ ግብዓቶች፣ቋሚና አላቂ ዕቃዎችን በተስማሚ ቦታ ማደራጀት ማለት ነው። **በካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍና ከሆነው** የማደራጀት ተግባር ጠቀሜታ የሚከተሉትን ለማስወገድ ይረዳል፦

- ዶክመንቶች፣ የሥራ ግብዓቶች፣ ቋሚና አላቂ ዕቃዎችን በአግባቡ ማደራጀት ለመፈለግ የሚባክን ጊዜን ያስቀራል፤
- ከመጠን በላይ የሆነ ክምችት በማስቀረት የቁሶች ጉዳትና አለግባብ ለንብረት የሚወጣን ወጪ ይቀንሳል፤
- አለአግባብ በግምጃ ቤት ውስጥ በማከማቸት ሰራተኞች ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳትን ይቀንሳል፤
- የሚፈለገውን ከማይፈለገው በመለየት የማይፈለገውን በአግባቡ በማስወገድ የሥራ አካባቢን ምቹና ሳቢ በማድረግ የሥራ ተነሳሽነትን ይጨምራል፤
- ተገቢውን ነገር በተገቢ ቦታና ሁኔታ ማስቀመጥ እና በግልጽ በማመልከት በቀላሉ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማስቻል ነው።

10.3. ማፅዳት-Shine

ሠራተኞች በሥራ ቦታ ካይዘንን በአግባቡ በመተግበር የሥራ ቦታን በተገቢው ሁኔታ ማደራጀትና ወጥ የሆነ አሰራርን በመዘርጋት የስራ ቦታችንንና የስራ መገልገያ መሳሪያዎቻችንን በማጽዳት እንዲሁም ያሉበትን ሁኔታ በመፈተሽ ጽዱ ማድረግ ማለት ነዉ። ተገቢውን ነገር በተገቢ ቦታና ሁኔታ ማስቀመጥ እና በግልጽ በማመልከት በቀላሉ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ማስቻል ነው። የስራ ቦታችን ፅዱ በሚሆንበት ጊዜ ማራኪ እና ሳቢ ስለሚሆኑ ሰዎች በቀላሉ እንዲጠቀሙዋቸዉ እና ስራችንን በደስተኛ መንፈስ ለመስራት ያስችለናል። ተቋሙን ጽዱ ማድረግ ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት ከመቻል ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለው።

ማፅዳት እና ፍተሻ ማካሄድ ተነጣጥለዉ ሊታዩ የሚችሉ አይደሉም። ምክንያቱም ፅዳት በሚካሄድበት ጊዜ የስራ መገልገያ መሳሪያዎቻችንን ደህንነት በተዘዋዋሪ ሊለሚፈተሽ ነው። ጽዳት ወይም ፍተሻን ማከናወን ሲባል የሥራ መሳሪያ መቀትን፣ በጣም መቀዝቀዙን፣ የለቀቀ ብሎን መኖሩንና አለመኖሩን በመዳሰስ መለየትን እንዲሁም የሥራ መሳሪያ ብናኝ ካለው፣ የማሽን መበላሸት ካለ፣ ከማሽኑ እቃ የጎደለ ካለ፣ የዘይት መፍሰ ካለ፣ የውሃ መፍሰስ ካለ በማየት መለየት እና ያልተለመደ ድምጽ ደግሞ በመስማት መለየት ያካትታል።

10.4. ማላመድ-Standardize

ማላመድ ማለት ከመጀመሪያዎቹ 3ቱ «ማ» ዎች በየዕለቱ የሚከናወኑ የካይዘን ተግባራት ማለትም ማጣራት፣ ማደራጀት እና ማጽዳት ጋር የተለየ ነው፣ የመጀመሪያዎቹ 3ቱ ማ ዎች የካይዘን ተግባራት ሲሆኑ ማላመድ ግን 3ቱን «ማ» ዎች ጠብቆ ለማቆየት የምንጠቀምበት ዘዴ ነው። ከላይ የተገለጹትን 3ቱን ማ ዎች ማጣራትን፣ ማደራጀትንና ማጽዳትን ለእያንዳንዱ ሠራተኛ እለታዊ ክንውን ሆኖ ከመደበኛ ሥራቸው ጋር የሥራ አካል ሆኖ በቀጣይነት እንዲከናወን ወጥ አሠራርን የመዘርጋት ዘዴ ነው። "Where there is no standard, there can't be kaizen" ይባላል።

10.5. ማዝለቅ-Sustain

ማዝለቅ ማለት ትክክለኛ እና አግባብነት ያላቸዉ ህጎችን አስጠብቆ የእለት ተእለት ተግባር በማድረግ ዘለቄታዊ እና ቀጣይነት ያለው አሰራር ማድረግ ነዉ። ከላይ የተገለጹት የ4ቱን ማ ዎች በሁሉም ሰራተኞች ደረጃ በቀጣይነት በሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና ተቋማዊ የአሰራር ባህል ማድረግ ነው። ይህ የማዝለቅ የካይዘን ፍልስፍና የሥራ አካባቢን ደረጃ እና ደንብ በመጠበቅ ዘላቂ ማድረግን ያጠቃልላል።

11. የካይዘን ዕቅድ ደረጃ ፍሰት ማደራጀት

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን ምቹና ሳቢ የሥራ አካባቢ በመፍጠር የተገልጋዮችን እርካታ ለማሳደግ መረጃ የሚሰበሰብበት፣ የሚተነተንበትና ደረጃ የሚሰጥበት አሠራር ለመዘርጋት የካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍናን በተቋሙ ለመተግበር አሁን ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ማወቅ ወይም መረዳት አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ካይዘንን ለመተግበር ዕቅድ በማቀድ የካይዘን አስተግባሪ ቡድን የሆነ ከልቡን በማደራጀት፣ የካይዘን ትግበራ ወሰኖችን በማውጣት፣ አስፈላጊ በጀት እና ግብ በማስቀመጥ የዕቅዱን መተግበር የግድ ይላል።

በዚሁ መሰረት ምቹና ሳቢ የሥራ አካባቢ እንዲሆን የቢሮ አደረጃጀቱ በካይዘን መርህ

መሠረት ቅልጥፍናን እና ወጪ ቆጣቢነትን ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ እቅድና አፈጻጸምን አስመልክቶ መመዘኛ መሰፈርቶችን በመቅረጽ እና ቼክ-ሊስት በማዘጋጀት የመገምገም፣ ሞዴል ፈፃሚ የሥራ ክፍልን የመለየትና የማበረታታት፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን የመቀመር እና የማስፋት ሥራ የሚተገበር ይሆናል ተብሎ ይታመናል።



ስዕል 1፡- ያልተደራጀ ንብረት ማካማቻ ክፍል



ስዕል 2፡- የኤሌክትሪክ ገመድ አጠቃቀም



ስዕል 3፡- የባለሙያ ጠረቤዛ





ስዕል 5፡- የባለመ·ያ ኮምፒዩ·ር



ስዕል 6፡- የፕሪንተር አቀማመጥና አጠቃቀም



ስዕል 7፡-

ስእል 9፡- የዶክመንቶች አቀማመጥ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን

ስዕል 10፡- ካይዘን ሲተገበር

ስእል 11፡- ካይዘን ሳይተገበርና ሲተገበር ሲነፃፀር



ስዕል 12፡- የፈለግነውን በቀላሉ ማግኘት እንችላለን

ስዕል 1
ማፅዳት







ስዕል 14፡- ከካይዘን ትግበራ በኃላ የሚያሳይ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የመንገስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን



የስራ ፍሰትን የሚያሳይ መዋቅራዊ አደረጃጀት(Organization stricture

ስዕል 15፡- ካይዘን ፈፃሚ የስራ ክፍሎች

12. የበጀት ዝግጅት

በባለስልጣኑ ውስጥ የካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍናን በአግባቡ ለመተግበርና ሥራ ላይ ማዋል Implementation ደረጃ ለአምስቱ ማ ዎች ትግበራ የገንዘብ ወጪ አስፈላጊ በመሆኑ በቂ በጀት በማስፈቀድ አስተባባሪ ግብረ ኃይሉ የሚያስፈልገውን ወጪ በመገመት ወደ ትግበራ መግባት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ ይታመናል።

13. የካይዘን ሥራ አመራር ትግበራ ክትትልና ድጋፍ

በባለስልጣኑ አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ለማሳለጥ ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች መካከል የለውጥ ትግበራ አካል አንዱ ከሆነው የካይዘን ትግበራ ክትትልና ግምገማ ሂደትን አጠናክሮ ማስኬድ ወሳኝ ጉዳይ ነው። የካይዘን ክትትልና ግምገማ ሂደቱ የለውጡ ዓላማና ግብ በትክክል መሳካቱን፣ እየተተገበረ መሆኑን፣ ወጭና ጥቅሙ የሚመጣጠን መሆኑን፣ የታቀዱት ተግባራት ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆኑ፣ ግብዓቶቹ እና ውጤቶቹ ምን ያህል እንደተሟሉ መገምገምን የመሳሰሉ ዋና ዋና ጉዳዮችን ያካትታል። በመሆኑም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት፣ ከሠራተኞች የሞራልና የሥራ ተነሳሽነት አንጻር የተደረጉ ለውጦች ምን ያህል ውጤቱ የተሳካ ወይም ያልተሳካ የሚሉ ጉዳዮችን ትኩረት ሰጥቶ የሚከናወን ተግባር መሆኑ ክትትል እንደሚያስፈልገው ይታሰባል።

በዚሁ መሰረት በመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የሚተገበረው የካይዘን ሥራ አመራር ፍልስፍና በሁሉም የሥራ ክፍሎች ሥር ያለው የተቋሙ ሠራተኞች የሚተገብሩት ሆኖ የተቋማዊ ሥራ አስፈፃሚ ደግሞ ካይዘን አንዱ የለውጥ መሳሪያ እንደመሆኑ መጠን በተቋም ደረጃ መተግበሩን አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት ይጠበቃል።